# የሚያልፍ ይለፍ እንጅ!....

*የሰው - ሰውነቴ፣ የ'ኔ ማንነቴ*

*የልቤ ትርታ - የሰራ አከላቴ፤*

*መጠሪያ ቋንቋዬ፣ ጌጤና ውበቴ*

*ኢትዮጵያ ነሽ እኮ ክብርና ሕይወቴ።..........*

ባልዋልኩበት ውሏል፣ ብለው ቢከሱኝም

ያለህግ - ያለፍርድ ቢወነጅሉኝም፤

ወህኒ-ቤት - ከርቸሌ፣ ቢያወርዱኝ ዘብጥያ

ቢገርፉ - ቢወግሩኝ፣ ከምሽት እስከ አጥቢያ፤

እኔ እንደሁ ወይ ፍንክች! የመጣው ቢመጣ

ከበጎ አላማዬ፣ ከእውነቴ ላልወጣ።

ከሰው ንብረት አልፈው ደም የሚጠማቸው

አሳር ቢያሳዩኝም በእኩይ ምግባራቸው፤

የህይወት ጉዞዬን ቢያደርጉት መራራ

በላዬ ቢከመር፣ ሀዘን - ከመከራ፤

በድን አያደርጉት ቆራጥ ህሊናዬን

አያቆሽሹትም ንፁህ - ብሩህ ልቤን።

ሀገር - ወገን ማለት ጠፍቶ ከውስጣቸው

ቢያሳክራቸው የስልጣን ጥማቸው፤

ምንም ምን ቢያደርጉኝ፣ ምንም ምን ብሆን

እኔ እንደሁ ወይ ፍንክች!.... አልሰጥም እጄን።

ተስፋና ምኞቴን ከግብ ሳላደርስ

የሚያግደኝ የለም አፈር እስክለብስ።

*የሰው -  ሰውነቴ፣ የ’ኔ ማንነቴ*

*የልቤ ትርታ - የሰራ አከላቴ*

*መጠሪያ ቋንቋዬ፣ ጌጤና ውበቴ*

*ኢትዮጵያ ነሽ እኮ ክብርና ህይወቴ።......*

**ልታረዝ - ልጠማ፣ ልዋረድ በዓለም ላይ**

**እንቅልፌ ይሁን መከራና ስቃይ፤**

**ልታደን እንደ አውሬ፣ ልሁን ምፃአተኛ**

**ልግረፍ - ልታሰር እንደ ወንጀለኛ፤**

**እጅ - እግሬ ይቸንከር፣ ይመታ ‘በካስማ’**

**ልጎተት በመሬት፣ እኔስ ልቁሰል ልድማ፤**

**ልወርወር ጫካ ውስጥ፣ ጥቅጥቅ ካለ ደን**

**የአውሬ መጫዎቻ፣ ምግባቸው ልሁን።**

**ደሜ እንደጎርፍ ውሀ ይውረድ እንደ ጅረት**

**ስጋዬም ይዘልዘል፣ ይጠበስ በእሳት፤**

**ወይም ካሰፈለገ፣ ቆዳዬ ይገፈፍ ስልቻ ይሰፉ**

**አጥንቴም ይፈጭ አንደ አመድ ይደፉ፤**

**ገሀነም - ሲኦል ትሁን ምድር ለ’ኔ ሕይወት**

**ብቻ**...............................................

**ብቻ**... **አልይ ውድቀትሽን፣ እኔ ያ’ችን ውርደት።**

**የሚያልፍ ይለፍ እንጂ፣ አ’ች አትለፊብኝ**

**ዛሬም**... **ለዘላዓለም**... **ኢትዮጵያ ኑሪልኝ**!!!

**------//------**

**ፊልጶስ /   ኢሜል፡philiposmw@gmail.com**

***መታሰቢያነቱ፤ ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለሰው ለጆች እኩልነትና ለሀገራቸው ለዕልናና ክብር ብለው በእሥር ቤት ለሚማቅቁና በትግል ላይ ለሚገኙ ወገኖቻችን።***